## የፓስፖርት አገልግሎት ለማግኘት ለሚትፈልጉ ኢትዮጵያውያን

- እባክዎ አገልግሎቱን አዘጋጅተን እንድንስጥዎ በጥንቃቄ አንብበው አስፈለጊውን ማስረጃዎች ከነ ፎቶ ኮፒያቸው አያይዘው ያቅርቡ/ይላኩ፡፡ በኢትዮጵያ ኢሚግሬሽን ሲሰጥ የነበረው አዲሱ ማሽን ሪደብል ፓስፖርት እ.ኤ.አ ኤፕሪል 2010 ጀምሮ በኢምባሲያችን በኩል አገር ቤት ተልኮ መሰጠት ስለተጀመረ እባክዎ ከጉዞ ቀን ወይም ከፓስፖርት እድሳት ጋር በተያያዘ አገልግሎት ለመጠየቅ ቢያንስ 3 ወር አስቀድመው ማመልከት ይጠበቅቦታል፡፡
- አዲሱ ማሽን ሪደብል ፓስፖርት ለማግኘት የጣት አሻራ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን ከዚህ ቀደሞ አዲሱን ፓስፖርት ሲወስዱ የጣት አሻራ ሰጥተው ከነበረ በድጋሚ መስጠት አያስፈልግዎትም፡፡ እድሜአቸው ከ14 አመት በታች የሆኑ ህጻናት አሻራ መስጠት አይጠበቅባቸውም፤ ሆኖም ከዚህ ቀድሞ ከ14 ዓመት በታች በመሆናቸው ምክንያት ያለ አሻራ አዱሱ ፓስፖርት ተዘጋጅቶላቸው ከነበረና አሁን ከ14ዓመትና በላይ ከሆኑ የጣት አሻራ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- ኢምባሲው ፓስፖርትዎን ለማዘጋጀት ተጨማሪ ማስረጃዎች እንዲያቀርቡ ሲጠይቅ እባክዎ በተነገረዎት በሳምንት ግዜ ውስጥ ማስረጃውን ይላኩልን፡፡

## አገልግሎቱ ያበቃ ፓስፖርት ለማሳደስ

*መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች*

1 አራት (4) የፓስፖርት መጠን ያለውና ቢያንስ ከ6ወር ወዲህ የተነሱት ፎቶግራፍ (ሁለቱ ጆሮዎች የሚታዩ፣ መደቡ ነጣያለና ከጀርባው ስም የተጻፈበት)

2 ለመቀየር ወይም ለማደስ የተፈለገው ዋናው ፓስፖርት ማቅረብ

3 ለመቀየር ወይም ለማደስ የተፈለገው ፓስፖርት መረጃ ያለበትን ማለትም ስም፣ ፎቶግራፍ፣ ፓስፖርቱ የተሰጠበትና ለመጨረሻ ጊዜ የታደሰበትን ገጽ የሚያሳይ በሁለት ኮፒ ማቅረብ

4 በጃፓን አገር ያሉበትን ስታተስ የሚያሳይ ማስረጃ በሁለት ኮፒ

- አሊያንስ መታወቂያ ኮፒ

5 የአገልግሎት ክፍያ 6050 የጃፓን የን በካሽ ወይም ባንክ ትራንስፌር

6 የጣት አሻራ ማቅርብ ለሚጠበቅባችሁ (ለማኑዋሉ የድሮ ፓስፖርት) በአቅራቢያዎ በሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ ወይም የጣት አሻራ ለመውሰድ ፈቃድ ካላቸው ድርጅቶች ዘንድ በመሄድ አሻራዎን ሰጥተው ዋናውንና ኮፒውን ማቅረብ/መላክ(በፖስታ ለሚልኩ አማልካቾች) ፣ በአካል ኤምባሲው ቀርበው ለሚያመለክቱ እዚያሁኑ መስጠት ይቻላል፡፡

7 ማመልከቻ ቅጽ በሁለት ኮፒ መሙላት

## በጠፋ ፓስፖርት ምትክ አዲስ ፓስፖርት ለመቀየር

*መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች*

**1** 4 የፓስፖርት መጠን ያለውና ቢያንስ ከ6ወር ወዲህ የተነሱት ፎቶግራፍ (ሁለቱ ጆሮዎች የሚታዩ፣ መደቡ ነጣያለና ከጀርባው ስም የተጻፈበት)

**2** ኢትዮጵያዊነትን የሚያስረዱ ሰነዶች በሁለት ኮፒ ማቅረብ

- የቀድሞ ፓስፖርት መረጃ ያለበትን ማለትም ስም፣ ፎቶግራፍ፣ ፓስፖርቱ የተሰጠበትና ለመጨረሻ ጊዜ የታደሰበትን ገጽ የሚያሳይ ማቅረብ ወይም
- በኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መስሪያቤት የተረጋገጠ የልደት ማስረጃ ወይም
- የቀበሌመታወቂያ

- መጥፋቱን የሚያረጋግጥ የፖሊስ መስረጃ

3 በጃፓን አገር ያሉበትን ስታተስ የሚያሳይ ማስረጃ በሁለት ኮፒ

- አሊያንስ መታወቂያ ኮፒ

4 የአገልግሎት ክፍያ 7,260 የጃፓነ የን በካሽ ወይም ባንክ ትራንስፈር

5 የጣት አሻራ ማቅርብ ለሚጠበቅባችሁ በአቅራቢያዎ በሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ ወይም የጣት አሻራ ለመውሰድ ፈቃድ ካላቸው ድርጅቶች ዘንድ በመሄድ አሻራዎን ሰጥተው ዋናውንና ኮፒውን ማቅረብ/መላክ (በፖስታ ለሚልኩ አማልካቾች) ፣ በአካል ኤምባሲው ቀርበው ለሚያመለክቱ እዚያሁኑ መስጠት ይቻላል፡፡

6 መጠየቂያ ቅጽ በሁለት ኮፒ መሙላት)

## ለመጀመሪያ ጊዜ ፓስፖርት ለሚጠይቁ

*መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች*

1 አራት(4) የፓስፖርት መጠን ያለውና ቢያንስ ከ6ወር ወዲህ የተነሱት ፎቶግራፍ (ሁለቱ ጆሮዎች የሚታዩ፣ መደቡ ነጣያለና ከጀርባው ስም የተጻፈበት)

2 ኢትዮጵያዊነትን የሚያስረዱ ሰነዶች በሁለት ኮፒ ማቅረብ

- በኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መስሪያቤት የተረጋገጠ የልደት ማስረጃ
- አዲስ በጃፓን ለተወለዱ ህጻናት፡-
  - በጃፓን ውጭ ጉዳይ መ/ቤት የተረጋገጠ የልደት ማስረጃ
  - አገልግሎቱ የጸና የወላጆች የፓስፖርት ኮፒ

3 በጃፓን አገር ያሉበትን ስታተስ የሚያሳይ ማስረጃ በሁለት ኮፒ

አሊያንስ መታወቂያ ኮፒ

4 የአገልግሎት ክፍያ 6050 የጃፓን የን በካሽ ወይም ባንክ ትራንስፈር

5 የጣት አሻራ ማቅርብ በአቅራቢያዎ በሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ ወይም የጣት አሻራ ለመውሰድ ፈቃድ ካላቸው ድርጅቶች ዘንድ በመሄድ አሻራዎን ሰጥተው ዋናውንና ኮፒውን ማቅረብ/መላክ (በፖስታ ለሚልኩ አማልካቾች) ፣ በአካል ኤምባሲው ቀርበው ለሚያመለክቱ እዚያሁኑ መስጠት ይቻላል፡፡

6 ማመልከቻ ቅጽ በሁለት ኮፒ መሙላት

ማሳሳቢያ፡- አገልግሎቱን ለማግኘት ክፍያውን በባንክ ትራንስፈር ማድረግ የሚትፈልጉ ከሆነ በቅድሚያ ለኤምባሲው ደውለው መረጃ ያግኙ፡፡